# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 21 ህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# ፌዴራሊዝም



# በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ የምርጫ ወረዳ ሥራ አስፈጻሚዎች ሥልጠና ይሰጣል

ኅዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎች መጪውን ሀገር አቀፍ ምርጫን በማስመልከት ለምርጫ ወረዳ ሥራ አስፈጻሚዎች ከኅዳር 5-8 ቀን 2012 ዓ.ም የመጀመሪያ ዙር ሥልጠና መስጠቱ ይታወሳል፡፡ የዚሁ ሥልጠና ሁለተኛ ዙር በዚህ ሳምንት መጨረሻ ሥልጠናው ባልተዳረሰባቸው ምርጫ ወረዳዎች ለሚገኙ ለሥራ አስፈጻሚ አባላት እንደሚሰጥ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ገለጸዋል፡፡

ሁለተኛ ዙር ላይ የሚሰጠው ሥልጠና የኢዜማ ምርጫውን ማሸነፍ ሀገራዊ ፋይዳው እና ሊገጥመን የሚችለው ዋና ዋና ተግዳሮቶች፣ ቀጣዩን ሀገራዊ ምርጫ በማስመልከት በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀው ሰነድን ማስተዋወቅ እና የምርጫ ወረዳ መዋቅሮች ምርጫውን በማስመልጀከት ማድረግ የሚገባቸው አጠቃላይ ዝግጅትን ዓላማ አድረጎ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

በሁለተኛ ዙር ሥልጠና በኦሮሚያ ምስራቅ ሸዋ ዞን አዳማ ላይ ከአስር የምርጫ ወረዳዎች፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ ላይ ስምንት ምርጫ ወረዳዎች፣ በምዕራብ አርሲ ሻሸመኔ ላይ ሰባት የምርጫ ወረዳዎች፤ በሰሜን ሸዋ ፍቼ ላይ ስድስት የምርጫ ወረዳዎች፤ ሀገረ ማርያም ላይ አራት የምርጫ ወረዳዎች፤ ሲዳማ ዞን በአዋሳ ከተማ አስራ አንድ የምርጫ ወረዳዎች፤ በጌዶኦ ዞን ዲላ ላይ አምስት የምርጫ ወረዳዎችን ያጠቃለለ ሥልጠና እንደሚሰጥ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

## ልዩ የእራት ግብዣ ከኢዜማ ጋር



# የመዋሀድ ሀሳብም ሆነ የተጀመረ ምንም አይነት ድርድር እንደሌለ ኢዜማ አስታወቀ

ኅዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



በአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 10 በተደረገ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ኢዜማና ብልፅግና ፓርቲ የሚዋሀዱበት ነገር የለም ሲሉ የኢዜማ መሪ ብርሀኑ ነጋ (ፕ/ር) ገለፁ፡፡ ጠንካራ ሀገራዊ ፓርቲ መኖሩ ለዴሞክራሲ ጥሩ መሆኑን ያወሱት ብርሀኑ የመንግሥትን ሥልጣን የያዘው ፓርቲን የሚገዳደር ጠንካራ ሀገራዊ ፓርቲ መኖር አለበት ብለን እናምናለን ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ከብልፅግና ፓርቲ ጋር በተለያዩ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ልዩነት እንዳለ የሚገልፁት መሪው፣ በፖሊሲዎቹ ላይም ክርክር እንደሚካሄድ አስረድተዋል፡፡ ሀገርን ወደፊት ለመውሰድ በሚደረገው ጥረት መተባበር ግዴታ መሆኑን የሚናገሩት ብርሃኑ፣ ከብልፅግና ፓርቲ ጋር ግን የመዋሀድ ሀሳብም ሆነ የተጀመረ ምንም ዓይነት ድርድር እንደሌለ ተናግረዋል፡፡

ኢዜማና ብልፅግና ፓርቲ ሊዋሀዱ ነው በሚል እየተናፈሰ የሚገኘውን ተባራሪ ወሬ በማስመልከት ሀሳባቸውን እንዲያካፍሉ ዜጎች መድረክ የጠየቃቸው የኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናትናኤል ፈለቀ፣ ኢዜማ ከምንም ነገር በላይ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረትና መዳበር እንደሚያስጨንቀው ገልፀው፤ ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ ጠንካራ አደረጃጀት ያላቸውና አማራጭ ሀሳብ ይዘው የሚፎካከሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አስፈላጊ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ ሰብሳቢው «ሁለቱ ፓርቲዎች (ኢዜማ እና ብልፅግና) ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ፉክክር በማድረግ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲዳብር የማድረግ ከፍተኛ ዕድል አላቸው፤ ይህን እድል ማክሰም አንፈልግም» ብለዋል፡፡

## አድራሻ


ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ፌደራሊዝም ስንል . . .

በድጋሜ የቀረበ

የዓለማችን 40% የሚሆነው ሕዝብ የሚኖረው ፌዴራል የመንግሥት መዋቅርን በሚከተሉ ሃያ አምስት ሀገራት ውስጥ ነው። እነዚህ ሃያ አምስት ሀገሮች ፌዴራል የመንግሥት መዋቅርን የመረጡበት የየራሳቸው ምክንያት አላቸው። ፌዴራል ሥርዓቶች እንደየተቋቋሙበት ሀገር የፖለቲካ ባህል፣ ታሪክና ማኅበራዊ አደረጃጀት ይለያያሉ። በአንዳንድ ሀገሮች ውስጥ ፌዴራሊዝም የሚፈጠረው የተለያዩ ሉዓላዊ መንግስታት ተወያይተው በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት ሲሆን በአንዳንድ ሀገራት ውስጥ ደግሞ ፌዴራሊዝም አንድን ሉዓላዊ ሀገር ከመበታተን አደጋ ለማዳን በህዝበ ውሳኔ ወይም በፓርላማ ስምምነት የሚፈጠር ሥርዓት ነው። የፌዴራሊዝም አቀንቃኞች ሀገራት ፌዴራል የመንግሥት መዋቅርን የሚመርጡት በሚከተሉት አምስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው ብለው ያምናሉ እነኝህም፣

1. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ሉዓላዊ ሀገራት በፌዴራል መዋቅር ሲተሳሰሩ ትልቅ የጋራ ገበያ ይኖራቸዋል፣
2. ጠንካራ የመከላከያ ተቋም ይኖራቸዋል፣
3. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ሀገራት በፌዴራሊዝም መዋቅር ተሳስረው አንድ ሀገር ሲሆኑ በሀገራቱ መካከል ጠላትነትና በጦርነት መፈላለግ አይኖርም፣
4. አንድ ወጥ የሆነ የውጭ ግኑኙነት ፖሊሲ ይኖራቸዋል፣
5. በጋራ የመልማትና የማደግ ችሎታቸው ከእጥፍ በላይ ይጨምራል።

እነዚህ የፌዴራሊዝም ጠንካራ ጎኖች እንዳሉ ሆነው ፌዴራሊዝም እንደ ኢትዮጵያ እራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በተነሳባቸው ዘውግ-ብዙና ህይማኖተ-ብዙ ሀገራት ውስጥ በአንድ በኩል ሕዝብ በአካባቢው እራሱን በራሱ ማስተዳደር የሚችልበትን ዕድል ይፈጥራል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙሃኑ ህዳጣኑን እንዳሰኘው የማይዘውርበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይፈጥራል።

## ፌዴራሊዝም እንዴት ይፈጠራል?

ሀገራት ከፌዴራሊዝም ጋር የሚተዋወቁት በሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና መንገዶች ነው።

### 1 ፡- አብረን እንኑር ፌዴራሊዝም (Coming together Federalism)

"አብረን እንኑር" ፌዴራሊዝም ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ሉዓላዊ ሀገራት ፍጹም በሆነ ፈቃደኝነት ላይ ተመሥርተው በአንድ የፌዴራል መንግሥት መዋቅር ስር ለመተዳደር ሲስማሙ የሚፈጠር የፌዴራሊዝም ዓይነት ነው። ሀገራት እንደዚህ ዓይነት ስምምነት ላይ የሚደርሱት ቀልጣፋ፣ውጤታማና ብቃት ያላው መንግሥት ለመመስረት፣ትልቅና ነፃ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር፣ ጠንካራ የመከላከያ ተቋም ለመገንትና በመካከላቸው ሊነሳ የሚችል ጦርነትንና የጦርነት ስጋትን ለማስወገድ ነው። አሜሪካ፣ ሲዊዘርላንድና አውስትራሊያ በ"አብረን እንኑር" ፌዴራሊዝም የተፈጠሩ ሀገራት ናቸው:: እንዲህ ዓይነቱ ፌዴራል ሥርዓት አንዴ ከተዋቀረ በኋላ ሌሎች ሉዓላዊ ሀገራት ጥያቄ በማቅረብ ሊቀላቀሉት ይችላሉ። ለምሳሌ የዛሬዋን አሜሪካ የመሠረቱት አስራ ሶስት ግዛቶች ብቻ ነበሩ፣ የተቀሩት 37 ግዛቶች የአሜሪካንን ፌዴራል ሥርዓት የተቀላቀሉት በተለያዩ ጊዜያት ነው።

### 2፡-ሀገር እናድን ፌዴራሊዝም (Holding Together Federalism)-

"ሀገር እናድን" ፌዴራሊዝም ስሙ እንደሚያመለክተው አንድን ሉዓላዊ ሀገር ከመበታተን አደጋ ለማዳን ሲባል በፖለቲካ ልሂቃኑ ስምምነት ወይም በፓርላማ ውሳኔ የሚፈጠር የፌዴራሊዝም ዓይነት ነው። ፌዴራሊዝም በዚህ ዓይነት መንገድ ሲፈጠር ሉዓላዊነት ከማዕከል ተቆርሶ ለክልሎች ስለሚሰጥና ይህንን ሉዓላዊነት ተከትሎ ክልሎች የራሳቸው የአስተዳደር ወሰን ስለሚኖራቸው እንዲህ ዓይነቱ ፌዴራል ሥርዓት ሲፈጠር ለክልሎች የሚሰጠው ሥልጣን ምን ያክል ነው የሚለውና በተለይ እያንዳንዱ ክልል የሚከለለው በምን መመዘኛ ነው የሚለው ጥያቄ በጣም አወዛጋቢና ገና ከጅምሩ በትክክል ካልተሠራ ሀገራትን እስከ ማፍረስ ስለሚያደርስ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። ብዙውን ጊዜ "ሀገር እናድን" ፌዴራሊዝም የሚፈጠረው አሃዳዊ የመንግሥት መዋቅር ባለባቸውና የመገንጠል ጥያቄ በተነሳባቸው ወይም የተለያዩ የማንነት ስብስቦች "እራሳችንን በራሳችን እናስተዳድር" የሚል ጥያቄ በሚያነሱባቸው ሀገራት ውስጥ ነው። "አብረን እንኑር" እና "ሀገር እናድን" ሁለቱም ሀገራት ወደ ፌዴራሊዝም የሚመጡባቸው መንገዶች ናቸው፣ በሁለቱ መንገዶች መካከል ያለው አንድ ትልቅ ልዩነት በ"አብረን እንኑር" መንገድ ተጉዘው ፌዴራሊዝምን የሚፈጥሩ ሀገራት በፌዴራል መዋቅር ከመተሳሰራቸው በፊት ሉዓላዊ የነበሩ ሀገራት መሆናቸው ነው::

በ"ሀገር እናድን" የሚፈጠረው ፌዴራሊዝም ግን አንድን ሉዓላዊ ሀገር ወደ ተለያዩ ክልሎች በመከፋፈል የሚፈጠር ፌዴራሊዝም ነው::
ህንድ፣ ኢትዮጵያና ቤልጀም የ"ሀገር እናድን" ፌዴራሊዝም ምሳሌዎች ናቸው።

## የፌዴራሊዝም ዓይነቶች

እያንዳንዱ ሀገር ፌዴራል የመንግሥት መዋቅርን የሚመርጥበት የራሱ ምክንያት አለው። ለዚህም ይመስላል ሁለት ፍጹም አንድ ዓይነት የሆነ ፌዴራል ሥርዓት የሚከተሉ ሀገራት የሉም እስኪባል ድረስ ፌዴራሊዝም በሀገራት ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን ቅርጹና ይዘቱ ይለያያል። ሆኖም ፌዴራል ሥርዓቶች

የቱንም ያህል ቢለያዩም አንድ ሀገር ፌዴራላዊ የመንግሥት መዋቅር ይከተላል የሚባለው “እራስን በራስ ማስተዳደር” እና “የጋራ አገዛዝ” የሚባለው እጅግ በጣም መሠረታዊ የሆነውን የፌዴራሊዝም እሴት ተግባራዊ ማድረግ ከቻለ ብቻ ነው።

ፌዴራሊዝም አንዳንድ ሀገራት ውስጥ “ራስን በራስ የማስተዳደር” ጥያቄ መልስ ነው፤ አንዳንድ ሀገራት ውስጥ ትልቅ የጋራ ገበያና ጠንካራ ኢኮኖሚ የመፍጠር ፍላጎት ውጤት ነው። አንዳንድ ሀገራት ውስጥ ደግሞ ፌዴራሊዝም በተለያዩ ቡድኖች መካከል ለሚነሱ ግጭቶችና አለመግባባቶች ዕልባት ለመስጠት የሚወሰን ውሳኔ ውጤት ነው።
ሀገራት ፌዴራል የመንግሥት አወቃቀርን የመረጡበት ምክንያት እንደሚለያይ ሁሉ የሚከተሉት የፌዴራል ሥርዓት አወቃቀርም ያንኑ ያህል ይለያያል። ለምሳሌ አውሮፓ ውስጥ ያለው ፌዴራሊዝምና ሰሜን አሜሪካ ውስጥ ያለው ፌዴራሊዝም የሚመሳሰሉበትም የሚለያዩበትም መንገድ አለ። እዚያው ሰሜን አሜሪካ ውስጥም ቢሆን አሜሪካና ካናዳ ውስጥ ያለው ፌዴራሊዝም አወቃቀሩ ይለያያል። አሜሪካ ውስጥ ሁሉም የፌዴራሉ አካላት ማለትም የፌዴራል ግዛቶች ተመሳሳይ ወይም እኩል የሆነ ሥልጣን ነው ያላቸው (Symmetric Federalism)። ካናዳ ውስጥ ግን አንዳንዱ የፌዴራል ግዛት ከሌላው የፌዴራል ግዛት የተለየ ሥልጣን አለው።ለምሳሌ አሜሪካ ውስጥ የሕዝብ ብዛቷ ከአንድ ሚሊዮን በታች የሆነችው ዋዮሚንግ ግዛትና ከሃምሳ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ካሊፎርኒያ በፌዴራል ስርአቱ ውስጥ ያላቸው ሥልጣን እኩል ነው። በአንጻሩ የካናዳ ሕገ መንግሥት ለአንዳንድ የፌዴራሉ ክልሎች (ለምሳሌ ኪዩቤክ) ከሌሎች የካናዳ ክልሎች የተለየና ከፍ ያለ ሥልጣን (Asymmetric Federalism) ይሰጣል።

ከዚህ በተጨማሪ ፌዴራላዊ የመንግሥት መዋቅርን በሚከተሉ የተለያዩ ሀገራት ውስጥ ሉዓላዊነት ከማዕከል ተቆርሶ ወደ ክልሎች የሚወርድበት መንገድ ይለያያል። በመሰረቱ ፌዴራሊዝም ያልተማከለ የአስተዳደር ስልት ነው፤ ያልተማከለ ሲባል ግን የአለመማከል ደረጃው ከሀገር ወደ ሀገር ይለያያል፡፡ በአንዳንድ ፌዴራል ስርአቶች ውስጥ ክልሎች ትልቅ ስልጣን አላቸው፤ ለምሳሌ አሜሪካ ውስጥ እያንዳንዱ ግዛት የራሱ ህገመግስት አለው ደግሞም የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ ሳይገባበት የራሱን የግብር፤ የልማት፤ የትምህርትና የጤና ፖሊሲ የማውጣት ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡ ህንድ ውስጥ እያንዳንዱ ግዛት የራሱ ህገ መንግሥት የለውም፤ ይህ ማለት ደግሞ ህንድ ውስጥ በማዕከላዊው መንግሥትና በክልሎች መካከል ያለው የሥልጣን ግንኙነት እንደ አሜሪካ የላላ አይደለም፤ ወይም የህንድ ፌዴራሊዝም ከአሜሪካ ፌዴራሊዝም በበለጠ መልኩ የተማከለ ፌዴራሊዝም ነው፡፡

ፌዴራሊዝምን የመንግሥት መዋቅራቸው አድርገው የተቀበሉ ሀገራት ሁሉ የሚመሳሰሉባቸው ሦስት ዋና ዋና ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ፌዴራል ሥርዓት ባለባቸው ቦታ ሁሉ “ራስን በራስ ማስተዳደር” እና “የጋራ አስተዳደር” (Self Rule & Shared Rule) አለ። ሁለተኛ- በፌዴራሊዝም ውስጥ የዜጎች ግዴታ ለሁለት የተያዩ አካላት ነው (ለክልል መንግሥትና ለማዕከላዊ መንግሥት) ሶስተኛ- ፌዴራል ሥርዓት ባለባቸው ሀገራት ውስጥ የሀገር መከላከልና የውጭ ግንኙነት ሥራዎች ለማዕከላዊው መንግሥት የተተዉ ሥራዎች ናቸው። በሁሉም ሀገራት ውስጥ በፌዴራሉ መንግሥትና በክልል መንግስታት መካከል ያለው ግኑኝነት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተተ ነው። የአንዳንድ ሀገራት ሕገ መንግሥት ለምሳሌ ጀርመንና አሜሪካ ውስጥ ሕገ መንግሥቱ በግልጽ ለፌዴራሉ መንግሥት ያልሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት የክልሎች ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሆነ ሕገ መንግሥቱ ውስጥ ተጠቅሷል። ካናዳና ህንድ ውስጥ ደግሞ ሕገ መንግሥቱ በግልጽ ለክልሎች ያልሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት የፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሆነ ሕገ መንግሥቱ ውስጥ ተደንግጓል። እንዲህም ሆኖ አንዳንዴ የፌዴራልና የክልል ሕጎች ሊጋጩ ይችላሉ፤ ይህ በሚሆንበት ግዜ የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የጸና ይሆናል።

## ለመሆኑ ፌዴራል የመንግሥት መዋቅር ወይም ፌዴራሊዝም ስንል ምን ማለታችን ነው?

ቀላል በሆነና በማያሻማ ቋንቋ “ፌዴራልዝም” ማለት የአንድን ሀገር ሉዓላዊነት በክልልና በማዕከል በመከፈል ህዝብ በክልል እራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት፤ በማዕከል ደግሞ የፖለቲካ ሥልጣንን ከሌሎች ክልሎች ጋር ተጋርቶ ሀገሩን በጋራ ማስተዳደር የሚችልበት መንግሥታዊ መዋቅር ነው።

ፌዴራሊዝም በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ሲጠነሰስ ጀምሮና ዛሬም ድረስ መሠረታዊ ሃሳቡ እራስን በራስ ከማስተዳደር ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ በአካባቢ እራስን በራስ ማስተዳደር (Self-Rule) እና በማዕከል የፖለቲካ ሥልጣንን መጋራት (Shared-Rule) የሚለው የፌዴራሊዝም መሠረታዊ መርህ ዛሬም አልተለወጠም፡፡ እንዲያውም ፌዴራሊዝም አድማሱን እያሰፋ በዘር፤ በሐይማኖትና በቋንቋ በተከፋፈሉ ማኅበረሰቦች ውስጥና በተለይ የማንነትና የመገንጠል ጥያቄ በተነሳባቸው ሀገራት ውስጥ ፍቱን መድኃኒት
መሆኑን ማስመስከር የቻለ የመንግሥት መዋቅር ነው። ፌዴራል የመንግሥት መዋቅር ባለባቸው ሀገራት ውስጥ የክልልና የማዕከል ሉዓላዊነት አለ፤ ሆኖም በሁሉም ክልሎች ውስጥ የሚኖረው ህዝብ የአንድ ሀገር ዜጋ ነው።

## ኢትዮጵያና ፌዴራሊዝም

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፌዴራል ሥርዓት ጋር የተዋወቀችውና ፌዴራሊዝም በሕገ መንግሥት ደረጃ እውቅና አግኝቶ የመንግሥት መዋቅር የሆነው በ1987 ዓ.ም ነው።ኢትዮጵያ ውስጥ ፌዴራል የመንግሥት መዋቅር ሲመሠረት ዘጠኝ ክልሎች አብረው ተመሥረተዋል። የኢሕአዴግ አገዛዝ እነዚህን ክልሎች ለመከለል የተጠቀመው መመዘኛ አንድ ብቻ ነው፤እሱም ብሄር ወይም ቋንቋ ነው። ከጋምቤላና ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውጭ ሰባቱ ክልሎች የሚጠሩት በክልሉ ውስጥ አብዛኛው በሆነው ብሄር ስም ሲሆን የአብዛኞቹ የሥራ ቋንቋም የዚሁ ብሄር ቋንቋ ነው፡፡ ከ1983 ዓ.ም እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ የቆየው የሽግግር መንግሥት ዛሬም ድረስ ከሚተችባቸው ትልልቅ ትችቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ዛሬ በሥራ ላይ ያለውና አንዳንድ ኃይሎች አንቀበለውም ወይም እኛን አይወክልም የሚሉት ሕገ መንግሥት ሲረቅና ሲጸድቅ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አላሳተፈም የሚል ነው። በእርግጥም በሀገር-ግንባታ (Nation Building) ሂደት ውስጥ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት ሶስት ተቋማት ማለትም የምርጫ ሥርዓት፣ የመንግሥት ቅርፅና የመንግሥት መዋቅር በሕገ መንግሥት

ደረጃ ሲነደፉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነዚህ የወደፊት ዕድሉን በሚወስኑ ትላልቅ ተቋማት ምሥረታ ሂደት ውስጥ ይህ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ትርጉም ያለው ተሳትፎ አላደረገም። አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ሲጸድቅ ሕዝበ ውሳኔ እንኳን አልተደረገበትም፡፡ በዚህ የተነሳ ዛሬም ተደጋጋሚ ጥያቄ ከሚነሳባቸው ጉዳዮች ውስጥ የፌዴራል ሥርዓቱ አወቃቀርና የሕገ መንግሥት መሻሻል ጉዳይ ግንባር ቀደሞቹ ናቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የአስተዳደር አካባቢዎች በዳግማዊ ምኒልክ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴና በደርግ ዘመነ መንግሥት የተለያየ ቅርጽና ስም ነበራቸው። ለምሳሌ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ(ቀኃስ) ዘመንና በመጀመሪያዎቹ አስር የደርግ ዓመታት ኢትዮጵያ አስራ አራት ጠቅላይ ግዛትና ክፍለ ሀገር ተብለው የሚጠሩ የአስተዳደር አካባቢዎች ነበሯት። እነዚህ የአስተዳደር አካባቢዎች በውስጣቸው ብዙ ብሔሮችን ያቀፉ ነበሩ። ለምሳሌ በወቅቱ ሲዳሞ ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ሀገር ውስጥ ቦረና፣ ሱማሌ፣ ወላይታ፣ ጌዲኦ፣ ሲዳማ፣ ጉጂ፣ ቡርጂና ኮይራ የሚባሉ ብሔሮች እንደዛሬው «ውጣልኝ» ሳይባባሉና አንዱ ሌላውን ሳያፈናቅል አብረው ይኖሩ ነበር። ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ከፍተኛ ዕልቂት የታየባት የሞያሌ ከተማ በቀኃስና በደርግ ዘመነ መንግሥት ሶማሌው፥ ኦሮሞውና ሌሎችም የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ኢትዮጵያዊያን በሰላም የሚኖሩባት ከተማ ነበረች። ሞያሌ ውስጥ የኦሮሞና ሶማሌ ግጭት የጀመረው የሞያሌ ከተማ የሶማሌና የኦሮሚያ ክልል ተብላ ለሁለት ከተከፈለች በኋላ ነው። ምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ኦሮሞና ሶማሌ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ ወላይታና ሲዳማ፣ ጌዲኦና ጉጂ፣ ምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ ቤንሻንጉልና አማራ መሳሪያ አንስተው አንዱ ሌላውን ማጥቃት የጀመሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ብሄርንና ቋንቋን መሰረት ያደረገው ፌዴራሊዝም በተገነባባቸው ባለፉት ሃያ ስምንት ዓመታት ውስጥ ነው።

ባለፉት ሃያ ስምንት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዋና ዋናዎቹ የፌዴራሊዝም ፖለቲካዊና ማኅበራዊ እሴቶች ተጠቃሚ ባይሆንም ፌዴራሊዝም ከሚባል የመንግሥት መዋቅር ጋር መተዋወቅ ችሏል። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሄር ተኮርም ሆኑ ህብረ-ብሄር ፓርቲዎች ኢትዮጵያን የመሰለ ትልቅና ህብረ-ብሄር አገር ለማስተዳደር ከፌዴራሊዝም የተሻለ ሌላ የመንግሥት አወቃቀር የለም የሚል የጋራ ስምምነት ያላቸው ይመስላል። ሆኖም የአስተዳደር አካባቢዎች (ክልሎች) ሲመሠረቱ በምን መመዘኛ መመሥረት አለባቸው በሚሉና በክልሎች ውስጥ በተለያየ የአስተዳደር እርከን የሚገኘው ህዝብ እራሱን እንዴት ማስተዳደር አለበት በሚሉ ሃሳቦች ላይ ጉልህ ልዩነቶች አሉ።

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፌዴራል ሥርዓት ብሄሮች እራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ይችላሉ የሚለውን መብት ነው ተግባራዊ ያደረገው እንጂ ሕዝብ በሚኖርበት አካባቢ እራሱ በመረጣቸው መሪዎች መተዳደር አለበት የሚለውን ዲሞክራሲያዊ መብት አያከብርም። ለምሳሌ አዲስ አበባን ጨምሮ ድሬደዋ፣ ሐዋሳ፣ ጂማ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱና ሻሸመኔን የመሳሰሉ ከተሞች የህብረ-ብሄር ኢትዮጵያዊያን ማዕከሎች ቢሆኑም በእነዚህ ከተሞች ውስጥ የሚኖረው ህዝብ እራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ ተከብሮለት አያውቅም።

ዴሞክራሲና ፌዴራሊዝም የማይነጣጠሉ ማኅበራዊ እሴቶች ናቸው። ዴሞክራሲ አሃዳዊ የመንግሥት አወቃቀር ባለባቸው ሀገራት ውስጥ ሊኖር ይችላል፡ ፡ ለምሳሌ ፈረንሳይ፣ ሆላንድና ስዊድን ዴሞክራሲ የሰፈነባቸው አሃዳዊ ሀገራት ናቸው። ፌዴራሊዝም ግን ያለዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም። ዴሞክራሲ ለኅብረተሰብ ያበረከተው ትልቁ ገጸ በረከት የፖለቲካ ሥልጣንን ከፈላጭ ቆራጭ አምባገነኖች መዳፍ ውስጥ ወጥቶ የህዝብ ንብረት እንዲሆን ማድረጉ ነው። ፌዴራሊዝም ለኅብረተሰብ ያበረከተው ትልቅ ስጦታ ደግሞ ሕዝብ የፓለቲካ ሥልጣንን በአካባቢውና በማዕከል እኩል እንዲጋራው ማድረጉ ነው። ፌዴራሊዝም በማዕከልና በክልል ደረጃ የተዋቀሩ መንግሥታት ያሉበት ሥርዓት ነው ሲባል እራስን በራስ የማስተዳደር መብት ተግባራዊ የሚሆነው በክልል ደረጃ ብቻ አይደለም። በየትኛውም የአስተዳደር እርከን ደረጃ (አውራጃ፣ ወረዳ፣ ከተማ) የሚገኝ ሕዝብ እራሱ በመረጣቸው መሪዎች የመተዳደር መብት አለው፥ ይህ መብት ደግሞ ከሚቀጥለው ምርጫ ጀምሮ መከበር ያለበት መብት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ እየተተገበረ ያለው ፌዴራል ሥርዓት ከዴሞክራሲ ጋር የማይተዋወቅና በክልሎች ውስጥ ብዙሀኑ ህዳጣኑን እንዳሰኘው የሚዘውርበት ፌዴራል ሥርዓት ቢሆንም ፌዴራሊዝም ከዴሞክራሲ ጋር በአንድ ላይ ሲቀርብ ኢትዮጵያን ለመሳሰሉ ሀገራት ፍቱን መድኃኒት መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። እንዲሁም ሆኖ ግን ፌዴራሊዝም በተለይ በ"ሀገር እናድን" መንገድ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም በሀገራት ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን የፌዴራል ክልሎቹ የሚመሰረቱበት መንገድ እጅግ በጣም ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፌዴራል ሥርዓት የተመሠረተበት መንገድ የተለያዩ ህዝቦችን አንድ ላይ ማኖር አልቻለም፣ ለአስተዳደር አመቺ አይደለም፣ በክልሎች መካከል ከፍተኛ የእድገትና የኑሮ ደረጃ ልዩነት አለ፣ ባጠቃላይ የፌዴራል ሥርዓቱ የተዋቀረበት መንገድ ለክልሎችም ሆነ ለሀገራዊ እድገት አመቺ አይደለም። የፌዴራል ክልሎችን ለመከለል የሕዝብ ብዛትን፤ የቆዳ ስፋትን፤ የመልማት አቅምን፤ የተፈጥሮ ሀብት ስርጭትን፤ ቋንቋን፤ የአስተዳደር አመቺነትን፤ የአብሮ መኖር ታሪክን፤የታሪክ ትስስርን እና ኩታ ገጠም አሰፋፈርን እንደ መመዘኛ መጠቀም ጠንካራ የፌዴራል ሥርዓት ከመፍጠር ባሻገር ለዘላቂ ሠላምና ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ አንድ ክልል ሲዋቀር አወቃቀሩ ለክልሉ ህዝብ ሰላምና መረጋጋት፣ ልማትና እድገት እንዲሁም የአስተዳደር ቅልጥፍና የሚያመች ሆኖ መገኘት አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ክልሎች ለየራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለአጎራባች ክልሎችና ባጠቃላይ ለሀገር ሰላም፥ መረጋጋትና የጋራ እድገት አመቺ መሆን በሚችሉበት ሁኔታ መዋቀር አለባቸው። ፌዴራል የመንግሥት መዋቅርን በሚከተሉ ሀገራት ውስጥ አንዱ ትልቅ ችግር በአንድ በኩል በክልሎች መካከል የሚታየው የተፈጥሮ ሃብት፥ የህዝብ ብዛት እና የቆዳ ስፋት ልዩነት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ልዩነቶች ተከትሎ የሚመጣው በክልሎች መካከል የሚታየው የእድገት አለመመጣጠንና የኑሮ ደረጃ ልዩነት ነው። ኢትዮጵያን በመሳሰሉ በ"ሀገር እናድን" መንገድ ፌዴራል ሥርዓትን በሚፈጥሩ ሀገራት ውስጥ ክልሎች ሲመሰርቱ የህዝብ ብዛትን፣ የቆዳ ስፋትንና የመልማት አቅምን እንደ ዋና መመዘኛ አድርገው ቢወስዱ እንዲህ ዓይነቱን ችግር ማስወገድ ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ለብሄሮች ክልል የመሆንም የመገንጠልም መብት ይሰጣል። እነዚህ መብቶች ተግባራዊ ሲሆኑ

ተያይዞ የሚመጣው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ሆኖም ሕገ መንግሥቱ መብት ይሰጣል እንጂ መብቱ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መፈጸም ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና መብቱ በሥራ ላይ ሲውል በሌሎች ላይ ስለሚያደርሰው አሉታዊ ተጽዕኖ የሚለው ብዙ ነገር የለም። ለምሳሌ ዛሬ የሲዳማን የክልል ጥያቄ ለመመለስ አስቸጋሪ የሚያደርገው ሕገ መንግሥቱ በአፈጻጸም ላይ ብዙ ዝርዝሮች ስለሚጎድሉት ነው። ሀዋሳ ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ የደቡብ ኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የባህል ማዕከል የነበረች ህብረ-ብሄር ከተማ ናት። ሀዋሳ ዛሬ ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ በሁሉም ዘርፍ የተጫወተው ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ስለዚህ የሲዳማ የክልል ጥያቄ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት አንደኛ የሀዋሳ የወደፊት ዕድል ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት፡፡ ሁለተኛ ሲዳማ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ውስጥ የሚኖረው ሲዳማ ያልሆነው ማኅበረሰብ የወደፊት ዕጣ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄም አጥጋቢ መልስ ማግኘት አለበት። ብሄሮች እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት አላቸው ማለት በክልላቸው የሚኖሩትን ህዳጣን የማኅበረሰብ ክፍሎችም አብረው ያስተዳድራሉ ማለት አይደለም። እንዲያውም ህዳጣን ቡድኖች ብዙሀን በሆኑባቸው ቦታዎች ሁሉ እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸው መጠበቅ አለበት። የዴሞክራሲ ትልቁ መርህ ህዳጣኑን ከብዙሀኑ የፖለቲካ ጡንቻ መጠበቅ ነውና ትልልቆቹ ብሄሮች በክልላቸው የሚኖሩ ህዳጣን ቡድኖችን መብት ከብዙሃኑ እኩል ማክበር ብቻ ሳይሆን መጠበቅም (Protect) አለባቸው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦች እንዳሏት ይነገራል። ሕገ መንግሥቱ ለሁሉም ብሄሮች እራስን

በራስ የማስተዳድር መብት ወይም ክልል የመሆን መብት ይሰጣል። ይህንን ሕገመንግሥታዊ መብት መሬት ላይ ካሉ የተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ሳናገናዝብ "መብት" ነውና ሁሉንም ብሄር ብሄረሰቦች ወደ ክልል ደረጃ እናሳድጋቸው ብንል፤ብሄሮቹ "ክልል" ለመሆን የፈለጉበን ምክንያት ፋይዳ ቢስ ያደርገዋል፡፡በተጨማሪነትም የማእከላዊው መንግስት ተቀጽላ ስለሚያደርጋቸው በብሄራዊ ደረጃ አስተዳደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል። በነገራችን ላይ አንድ ብሄር እራሴን በራሴ ባስተዳድር ይሻለኛል ብሎ ክልል የመሆን ጥያቄ ሲያቀርብ ምንም አልነው ምን ጥያቄው የማንም ጥገኛ ሳልሆን የራሴን እድል በራሴ መወሰን እችላለሁ የሚል ነው። ሆኖም ይህ "የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን" ጥያቄ ያቀረበ ሕዝብ ክልል ከሆነ በኋላ በሁሉም ነገር የፌዴራሉ መንግሥት ጥገኛ ከሆነ መጀመሪያውኑ ጥያቄውም፤ ጥያቄው የተስተናገደበት መንገድም ትክክለኛ አልነበረም ማለት ነው። እዚህ ላይ አንድ መገንዘብ ያለብን ትልቅ ቁም ነገር አለ፡፡

አንድ ህዝብ እራሱን በራሱ ያስተዳድራል የሚባለው ክልል ስለሆነ ብቻ አይደለም። አንድ አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ያለው ብሄር ወይም የባህል ስብስብ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ የትምህርት ፖሊሲውን ባጠቃላይ አስተዳደራዊ ጉዳዮቹን በተመለከተ በክልል ውስጥም ሆኖ "የራስ ገዝ" (Regional Autonomy) መብት ተሰጥቶ እራሱን በራሱ ማስተዳደር ይችላል።

ኢትዮጵያ ለብዙ ሺ አመታት ሉዓላዊነቷ ተከብሮ የኖረች ሀገር ስለሆነች ኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጠር የሚችለው ፌዴራሊዝም "ሀገር እናድን" ፌዴራሊዝም (Holding Together Federalism) ብቻ ነው። በዘርና በቋንቋ በተከፋፈሉ ሀገራት ውስጥ የፌዴራሊዝም ተቀዳሚ ተግባር ልዩነቶችን ማስወገድና ግጭቶችን ማብረድ ሆኖ ሳለ ጭራሽ የፌዴራል ሥርዓቱ የተገነባው በዘርና በቋንቋ ልዩነቶች ላይ ተመስርቶ ከሆነ እንደዚህ ዓይነቱ ፌዴራሊዝም ለልዩነቶችና ለአለመግባባቶች ህጋዊ ሽፋን ከመስጠት አልፎ ጠንካራ የሀገር አንድነት መፍጠር አይችልም። የፌዴራል ክልሎች ድንበር የሚከለለው በዘርና በቋንቋ ላይ ብቻ ተመስርቶ ከሆነ ይህ ድንበር የአለመግባባቶችና የግጭቶች መንስኤ እንደሆነ ይኖራል እንጂ ሰላምና መረጋጋትን መፍጠር አይችልም።

**‹‹የፌዴራል ሥርዓቱ የተገነባው በዘርና በቋንቋ ልዩነቶች ላይ ተመስርቶ ከሆነ እንደዚህ ዓይነቱ ፌዴራሊዝም ለልዩነቶችና ለአለመግባባቶች ህጋዊ ሽፋን ከመስጠት አልፎ ጠንካራ የሀገር አንድነት መፍጠር አይችልም።››**

ዘርና ቋንቋን የመነሻ መሠረቱ ያደረገ ፌዴራሊዝም የእርስ በእርስ ግጭት ምንጭ መሆኑን ለመገንዘብ ያለፈውን ሃያ ስምንት አመታት ታሪካችንን ወደ ኋላ ዞር ብሎ ማየት ይበቃል። ኢትዮጵያ ውስጥ የዘውግ ፌዴራሊዝም ከተፈጠረ በኋላ በሶማሌና በኦሮሞ፣ በኦሮሞና በሀረሬ፣ በኦሮሞና በአፋር፣ በቦረናና በጋሪ፣ በጉጂና በጌዲኦ፣ በአማራና በኦሮሞ፣ በወላይታና በሲዳማ፣ በቤኒሻንጉልና በአማራ ብሄረሰቦች መካከል የተነሱት ግጭቶች የብዙ ሰላማዊ ዜጎችን ህይወት ቀጥፏል። እነዚህ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ብሄረሰቦች ቁጥር ከአስር ላይበልጥ ይችላል፤ ነገር ግን እነዚህ አስር ብሄረሰቦች ከሰማኒያ በመቶ በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ አቅፈው መያዛቸው መረሳት የለበትም።

የዘውግ ፌዴራሊዝም ሌላም ብዙ ችግሮች አሉበት፡፡ የአንድ ፌዴራል ሥርዓት መሰረቱ ቋንቋና ማንነት ሲሆን የፖለቲካ ሥርዓቱም የሚመሠረተው በቋንቋና በማንነት ላይ ይሆንና በእነዚህ ሀገራት ውስጥ ፓርላማውን ጨምሮ ብዙዎቹ ተቋሞች "ማንነት" የሚንጸባርቅባቸው ቦታዎች ይሆናሉ፡፡ በተቋም ደረጃ "ማንነት" ጎልቶ በሚታይባቸው አገሮች ውስጥ በዜግነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ሀገራዊ አንድነትና ብሄራዊ ስሜት መፍጠር አስቸጋሪ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ዘውግ-ብዙና ሐይማኖት-ብዙ ሀገራት ውስጥ የፌዴራሊዝም ተቀዳሚ ተግባር የተለያየ ቋንቋ፣ ባህልና ሐይማኖት ያላቸውን ሕዝቦች አስማምቶና አግባብቶ ብሄራዊ አንድነትንና ጠንካራ ሀገራዊ ስሜትን መፍጠር ነው። ይህንን ማድረግ የሚቻለው በኢኮኖሚ አብረው መልማት የሚችሉ ቦታዎችንና እንዲሁም፤የቦታ ቅርበት፤ የታሪክ ትስስርና ለአስተዳደር አመቺ በሆኑ ቦታዎች የሚኖሩ ህዝቦች እንዲቀራረቡና አብረው እንዲኖሩ በማድረግ ነው።

# በአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 12/13 ሕዝባዊ ስብሰባ ተደረገ

ኅዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

በአዲስ አበባ የምርጫ ወረዳ 12/13 የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) በተገኙበት ኅዳር 21 ቀን 2012 ዓ.ም ሕዝባዊ ስብሰባ አደረገ፡፡

በሕዝባዊ ውይይቱ ወቅት የኢዜማ መሪ «ከምርጫ 97 በኋላ የጀግኖች ሰፈር ፈረንሳይ ለጋሲዮን ስለመጣሁ ደስ ብሎኛል፤ ዛሬ የተገኘሁት የፈረንሳይ ለጋሲዮን ህዝብ በ97 ምርጫ ላደረገው ከፍተኛ ትግል ምስጋና ለማቅረብም ጭምር ነው፡» በማለት ለፈረንሳይ ለጋሲዮን ህዝብ ምስጋናቸውንና አድናቆታቸውን ገልጸዋል፡፡

የዕለቱን ውይይት የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 12/13 ሰብሳቢ የሆኑት ያሬድ አለማየሁ በምርጫ ወረዳው ላይ ስለተሠሩ የተለያዩ ሥራዎች ለታዳሚው ጠቅለል ባለ መልኩ አቅርበዋል፡፡ በንግግራቸው መቋጫ ላይም «ሀገሬን በማለቱ የዜግነት ፖለቲካን በማራመዱ የፈረንሳይ ለጋሲዮንና አካባቢው ሕዝብ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል፡፡ ለዚህም ዋጋ ለከፈላችሁ ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ አሁንም ኑ! ሀገርን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እናሻግር» በማለት ሀገራዊ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡



ከታዳሚው ስለቀጣዩ ምርጫ፣ ስለ አዲስ አበባ ጉዳይ፣ ስለኢዜማ ፖሊሲ የመሳሰሉት ጥያቄዎች ተጠይቀው ከኢዜማ አመራሮች ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ቀጣዩ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እንደሚሆን ኢዜማ ተስፋ እንደሚያረግ፤ ለዚህም ደግሞ ምርጫ ቦርድ በመምራት ላይ የሚገኙት ኃላፊ ከዚህ በፊት ለሀገር እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዋጋ የከፈሉ እንደሆኑ በማስታወስ የቦርዱን ኃላፊነት በቅንነትና በታማኝነት የማስፈጸም አቅም አላቸው ብሎ ኢዜማ እንደሚያምን አመራሮቹ ገልጸዋል፡፡ በአዲስ አበባ ጉዳይ ኢዜማ ከዚህ በፊት በተለያየ መድረክ ሲገልጸው እንደነበረው ከጋዜጠኛና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች እስክንድ ነጋ ጋር የአቋም ልዩነት የለውም ብለዋል፡፡

ኢዜማ የተሻለ ፓርቲ ሆኖ ለመውጣት የራሱን ፖሊሲ በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኝ ምርጫው ሲደርስ ፖሊሲውን ለሕዝቡ በይፋ በማሳወቅ ወደ ምርጫ ፉክክር እንደሚገባ እና ተመሳሳይ ውይይቶች ከምርጫ ወረዳ 12/13 ነዋሪዎች ጋር ኢዜማ እንደሚያደርግ ሊቀ መንበሩ የሺዋስ አሰፋ ለታዳሚው ገልጸዋል፡፡

# ኢዜማ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ ለማሸነፍ ያለውን ብቃት በማስመልከት በምርጫ ወረዳዎች ላይ ምዘና ሊያካሂድ ነው

ኅዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከተመሠረተ ጀምሮ ባደራጃቸው ከ400 በላይ በሚሆኑ የምርጫ ወረዳዎች ምርጫን ለማሸነፍ ያላቸውን ብቃት ለማረጋገጥ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ የምዘና እና የማረጋገጥ ሥራ እንደሚሠራ ታወቀ፡፡

በድርጅት ጉዳይ በኩል የሚሰበሰበው የምዘና እና የማረጋገጥ ሥራ የምርጫ ወረዳዎች ላይ ያለው የብቃት ደረጃ መገምገምና በቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ ለማሸነፍ ያላቸውን ብቃት ማረጋገጥን ዓላማ ያደረገ ሲሆን ምርጫን ለማሸነፍ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልደረሱ ወረዳዎች ካሉ የምርጫ ወረዳዎቹን በልዩ ትኩረት የማጠናከር ወይንም መልሶ የማደራጀት ሥራ ለመሥራት እና በምርጫ ወረዳዎቹ ላይ የጎደለ ካለ በሚቀጥሉት ሁለት ወራቶች ሙሉ ለሙሉ እንዲሟላ ለማድረግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የታቀደው ምዘናና ሥልጠና የሚካሄደው በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም፣ በአዊ ዞን፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር እንዲሁም ከባህርዳር ዙሪያ ለተውጣጡ ባህርዳር ላይ፤ ከሰሜንና ከደቡብ ወሎ እንዲሁም ከሰሜን ሸዋ ተመርጠው ለመጡ ደሴ ከተማ ላይ፤ ወላይታን ጨምሮ ሀዲያና ከንባታ፣ ከጎፋ ዞን፣ ከዳውሮና ኮንታ ዞን ለመጡ ወላይታ ላይ፤ ከጋሞ፣ ሰገል ዞንና ከደቡብ ኦሞ ዞን ለተውጣጡ አርባ ምንጭ ላይ፤ ከቤንች ማጂ ዞን፣ ከከፋ፣ ከጉራጌና ወራቤ እንዲሁም ከወልቂጤ ዞኖች ለመጡ ደግሞ ሚዛን አማን ላይ የምዘና ሥራ እንደሚሠራ፤ ምርጫን ለማሸነፍ የሚረዳም ተጨማሪ ሥልጠና እንደሚሰጥ ታውቋል፡፡